# የኢዴፓ የፖለቲካ ፕሮግራም

## መግቢያ

ኢዴፓ በተለያዩ አገራዊ ጉዳዮች የሚያራምዳቸውን አቋሞችና በአጠቃላይም የሚከተለውን ርዕዮተ ዓለማዊ አቅጣጫ ለአባላቱ፣ ለደጋፊዎቹና ለመላው የአገሪቱ ሕዝብ ለማስተዋወቅ በማሰብ ይህን የፖለቲካ ፕሮግራም አዘጋጅቶ አቅርቧል።

አገራችን ኢትዮጵያ የአንድ ብቸኛ ማኀበረሰብ ወይም ባህላዊ ሁኔታ መገለጫ ሳትሆን፣ በአገሪቱ ለሚኖሩ የተለያዩ ባህል፣ ቋንቋ፣ ኃይማኖትና ሌሎችም መለያዎች ያላቸው ሕዝቦች የአብሮነት መገለጫ የሆነች ታሪካዊ አገር ነች። አገራችን ባለፈችበት ረዥም ታሪካዊ ሂደት በርካታ በጎና የሚያኮሩ ገፅታዎች ያሉዋት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚያው መጠን ዛሬ ዓለማችን ከደረሰችበት ቁሳዊም ሆነ ስነ-ልቦናዊ የእድገት ደረጃ አንፃር ሲመዘን የሚያሳዝንና የሚያስቆጭ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ትገኛለች። በአሁኑ ወቅት አገራችን በመጨረሻው የድህነት ወለል ላይ የምትገኝ በመሆንዋ ምክንያት በዓለም ሕዝብ ፊት በረሃብ፣ በጦርነትና በአጠቃላይም በኋላቀርነት የምትታወቅ አገር ሆናለች።

አገራችን ከዚህ ዓይነቱ የድህነትና የጦርነት አዙሪት ወጥታ በተቻለ ፍጥነት ወደሰላምና ብልፅግና ጎዳና መግባት የሚጠበቅባት ቢሆንም እስከአሁን ድረስ ወደዚህ ዓይነቱ ተገቢ አቅጣጫ በአስተማማኝ ሁኔታ የሚያስገባት አዲስ የፖለቲካ ስርዓትና ባህል መፍጠር አልቻለችም።

ዛሬም በ21ኛው ክፍለ ዘመን ኢኮኖሚያችን የኋላቀር ግብርና ጥገኛ ሆኖ የቀጠለ ሲሆን ከሌላው ዓለም በተቃራኒም ከ85% በላይ የሆነው ሕዝባችን በዚሁ ኋላቀር ግብርና ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ኑሮ የሚተዳደር ነው። አገራችን እጅግ በከፋ ሁኔታ ስራ አጥነት፣ በሽታ፣ እርሃብ፣ እርዛትና መኃይምነትን የመሳሰሉ በርካታ ማኀበራዊ ችግሮች ተንሰራፍተው የሚገኙባት አገር ስትሆን ወደፊት ከእነዚህ መሠረታዊ ችግሮች ለመላቀቅ ዋስትና የሚሆናት የተረጋጋ ፖለቲካዊ ሁኔታ ገና አይታይባትም።

በአገሪቱ የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች እስከአሁን ገና በጋራ አገራዊ ጉዳዮቻቸው ብሔራዊ መግባባት ያልፈጠሩና ዛሬም እንደትናንቱ በጠላትነት ዓይን የሚተያዩና እርስ በርስ መጠፋፋት የሚፈልጉ ናቸው። አንዱ ፓርቲ ለሌላው ተገቢውን እውቅናና አክብሮት ሰጥቶ በጋራ አገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ አብሮ ለመስራት የሚችልበት፣ ሁሉም የአገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች ለአለፉት የአገሪቱ ችግሮችም ሆነ ለወደፊቱ የአገሪቱ መፍትሄዎች የጋራ ተጠያቂነትና ኃላፊነት ያላቸው መሆኑን አምነው የሚቀበሉበት፤ ከጭፍን ጥላቻና ፍረጃ በፀዳ መልኩ ምክንያታዊ ፖለቲካ የሚያራምዱበት ሁኔታ ገና አልተፈጠረም።

እነዚህ መሠረታዊ የአገራችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኀበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮቻችን ዘለቄታዊ መፍትሄ እንዲያገኙ በማሰብ ኢዴፓ በፓርቲነት ተቋቁሟል። ኢዴፓ ከእስካሁኑ የአገራችን ጥንፈኛና በጥቻላ የተሞላ የፖለቲካ ባህል በተለዬ በምክንያት የመደገፍንና በምክንያት የመቃወምን የፖለቲካ ባህል በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ ለመትከል የሚታገል ፓርቲ ነው። ኢዴፓ በእስካሁኑ የአራችን ፖለቲካ በተካረረ ሁለት ጥንፍ፣ ማለትም በገዥነትና በተቃዋሚነት መስፈርት-ብቻ ሲካሄድ ከኖረው የፖለቲካ ስልት በተለዬ ሁኔታ ፍፁም ሰላማዊ የሆነ፣ ለሌሎችም የፖለቲካ ኃይሎችና አገራዊ ተቋማት እውቅና በመስጠት የሚያምን፣ ብሔራዊ መግባባትን የመፍጠርና በጋራ አገራዊ ጉዳዮች አብሮ የመስራት ፖለቲካን የሚያራምድ 3ኛ የፖለቲካ አማራጭ ኃይል ሆኖ ለሕዝቡ ምርጫ እራሱን አቅርቧል።

ኢዴፓ የግለሰብን መብት ቀዳሚና መሠረት በማድረግ በአገራችን የቡድን መብቶች መከበር ይገባቸዋል ብሎ የሚያምን ሲሆን ኢትዮጵያውያን እራሳቸውን በራሳቸው ማስተዳደር እንዲችሉ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥርና በመንግስት መዋቅሮች ዘንድ ተገቢ የእርስ በርስ ቁጥጥርና ሚዛናዊነት እንዲኖር የሚያስችል ፌዴራላዊ አደረጃጀትን ይደግፋል።

ከኢኮኖሚያዊ አስተሳሰብ አኳያ ኢዴፓ በሂደት የካፒታሊስት ስርዓትን በአገራችን ለመገንባት የሚያስችልን የገበያ ኢኮኖሚ ስርዓትን የሚያራምድ ሲሆን በአሁኑ ወቅት አገሪቱ በምትገኝበት ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ምክንያት በኢኮኖሚው

ውስጥ መንግስት በሕግ የተገደበ ጊዜያዊ ተሳትፎ ሊኖረው ይገባል ብሎ ያምናል። በሂደት የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ እየተጠናከረና የገበያ ውድድር በአራችን እያሰፋ ሲመጣ መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ የሚኖረውን ተሳትፎ ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ እየለቀቀ መምጣትና የገበያ ኢኮኖሚ ስርዓትን ሙሉ በሙሉ የማስፈን ኃላፊነት ይጠበቅበታል ብሎ ያምናል። አገራችን ልታራምደው የሚገባውን ስትራቴጂ ለግብርናው፣ ለኢንዱስትሪውም ሆነ ለአገልግሎት የኢኮኖሚ ዘርፍ ተገቢና ተመጣጣኝ ትኩረት በመስጠት እርስ በእርስ የሚመጋገብና የሚደጋገፍ ቀጣይነት ያለውን ሚዛናዊ የሆነ እድገት የሚያመጣ መሆን ይገባዋል ብሎ ያምናል። በአገራችን ቁልፍ የኢኮኖሚ ጥያቄ የሆነውን የመሬት ስሪትን በተመለከተም ኢዴፓ የግል፣ የወልና የመንግስት የመሬት ይዞታን እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ የሚያደርግ አማራጭ ያራምዳል።

በአጠቃላይ ኢዴፓ የሚያራምደው ርዕዮተ ዓለም የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባና ከአገሪቱ ተለዋዋጭ ሁኔታዎች ጋር እራሱን እያጣጣመ መጓዝ የሚችል ዘመናዊ የሊበራል ዴሞክራሲ አስተሳሰብ ነው። ኢዴፓ በሁሉም ዘርፍ ወሳኝ ተሳትፎና ሚና ያለው መካከለኛ ገቢያለው ሕብረተሰብ (Middle class) ባልተፈጠረባትና የግል ክፍለ ኢኮኖሚ ገና በበቂ ሁኔታ ባልተስፋፋባት ኢትዮጵያ ሊበራል ዴሞክራሲን በአጭር ጊዜ ተግባራዊ ማድረግ እንደማይቻል ቢገነዘብም የአገሪቱ የወደፊት መድረሻ በሊበራል ዴሞክራሲ አስተሳሰብ እንዲመራ የሚያስችለውን አቅጣጫ ከወዲሁ ይከተላል። ኢዴፓ ከሚያራምዳቸው አጠቃላይ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አስተሳሰቦች አኳያ ሲመዘንም ርዕዮተ- ዓለማዊ አሰላለፉ መካከለኛ ቀኝ ዘመም (center right) ነው።

# ክፍል I
# የፖለቲካ ሥርዓት

## 1. የመንግሥት መዋቅር

ኢትዮጵያ የሚከተሉት በሕገ መንግሥቱ ውስጥ ሥልጣናቸው በዝርዝር የሚገለጽ በሁለት ደረጃዎች የተከፈሉ መንግሥታዊ መዋቅሮች ይኖሯታል። እነሱም፤ የፌደራል መንግሥት እና የራስ አስተዳደር ክልል መንግሥት ናቸው።

## 2. የመንግሥት ቅርንጫፎች

የፌዴራሉም ሆነ የራስ አስተዳደር ክልል መንግሥት ሶስት የመንግሥት ቅርንጫፍ አካሎች ይኖራቸዋል። እነሱም፤ ሕግ አውጭ፣ ሕግ አስፈጻሚ እና ሕግ ተርጓሚ ናቸው።

## 3. የመንግሥት አመሰራረት መርሆዎች

3.1 የመንግሥት የፖለቲካ ሥልጣን ከሕዝብ ፈቃድ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲመነጭና በሕግ የበላይነት እንዲመራ ይደረጋል።

3.2 የብዙሃን-ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን እውን ለማድረግ፣ በሕዝብ ቀጥተኛ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ፣ በነፃና ፍትሃዊ የምርጫ ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል።

3.3 ኢትዮጵያ የራስ በራስ አስተዳደር ስልጣን ያላቸው ክልሎችን ያካተተ ፌዴራላዊ አደረጃጀት ይኖራታል።

3.4 የክልሎች አደረጃጀትም በሕዝብ ብዛትና በቆዳ ስፋት ተመጣጣኝነት ባለው ሁኔታ፤ ታሪካዊና ባህላዊ ትስስርን፣ ቋንቋን፣ የህዝብ አሰፋፈርን፣ የመልክዓ ምድር አቀማመጥን፣ የአስተዳደርና የልማት አመቺነትን ባካተተ መልክ እንዲደራጅ ይደረጋል። እነዚህን ሁኔታዎች በተናጠል ወይም በጋራ ባገናዘበ መልኩ የራስ በራስ አስተዳደርን መብትና ነፃነት በማረጋገጥ ሕዝቡ የራሱን አስተዳደር እንዲረከብና ሕይወቱን እንዲመራ ይደርጋል።

3.5 በፌደራል መንግሥትና በራስ አስተዳደር ክልሎች፤ እንዲሁም በራስ አስተዳደር ክልሎች መካከል የሚኖረው ግንኙነት፣ ልዩነት፣ ተዛምዶ፣ አሰራር፣ የሥልጣን ገደብ ወ.ዘ.ተ በሕገ መንግሥቱ ይደነገጋል።

3.6 ኢዴፓ ሰላማዊ በሆነ የትግል ስልት በጽኑ ያምናል። ስለሆነም፣ የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥ ወይም የፖለቲካ ሥልጣን ሽግግር ሰላማዊና ቀጥተኛ በሆነ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ አማካይነት ብቻ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተራ ሥልጣን የሚይዙበትና ከሥልጣንም የሚወርዱበት ዴሞክራሲያዊ ባህል እንዲዳብር በጽኑ ይታገላል።

# ክፍል II

# ፖለቲካዊ ጉዳዮች

## 4. ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች

4.1 እ.ኤ.አ በዲሴምበር 10 ቀን 1948 ዓ.ም. በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ የጸደቀው የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ ቁጥር 217 ኤ/111 እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ የተባበሩት መንግሥታትና የአፍሪካ ሕብረት የሰብአዊ መብት ውሎችና ስምምነቶች ሁሉ በኢትዮጵያ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል።

4.2 የማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በማንኛቸውም የሀገሪቱ አካባቢዎች ተንቀሳቅሶ የመሥራት፣ የመኖር፣ በግሉም ሆነ በጋራ ንብረት የማፍራት፣ የመጠቀም፣ የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የመውረስና የማውረስ መብቱ ይጠበቃል።

4.3 የማናቸውም ሰው የመኖር፣ የመናገር፣ ሃሣብን በጽሑፍ የመግለጽ፣ የመደራጀት፣ የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ድጋፍ ወይም ተቃውሞ የማድረግ፣ ሥራ የማቆም፣ እንዲሁም ከመገረፍ፣ ከመሰቃየት፣ በሰውነትም ሆነ በአዕምሮ ላይ ከሚደረግ ጥቃት የመጠበቅ፣ ያለ ፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከመታሰር፣ ሰውነቱም ሆነ ንብረቱ ከመፈተሽ፣ በግዳጅ ከመመርመርና ከመሳሰሉት ጥቃቶች የተጠበቀ ይሆናል።

4.4 ማንኛውም ዕድሜው ለፖለቲካ ተሳትፎ የደረሰ ኢትዮጵያዊ በሕግ የታገደ እስካልሆነ ድረስ የመምረጥና የመመረጥ መብቱ የተጠበቀ ይሆናል።

## 5. የብሔር/ብሔረሰቦች እኩልነት

ኢትዮጵያ የአያሌ ብሔር/ብሔረሰቦች አገር እንደመሆኗ የተለያዩ ባህሎችና ቋንቋዎች በእኩል ደረጃ የሚከበሩባት፣ የብሔር/ብሔረሰቦች እኩልነት የተረጋገጠባት አገር ትሆናለች። መንግሥት ሁሉም ብሔር/ብሔረሰቦች ባህላቸውንና ቋንቋቸውን በእኩልነትና በነፃነት እንዲያዳብሩ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል። የኢትዮጵያ ብሔር/ብሐረሰቦች በአገሪቱ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ያለምንም አድልዎ ጉልህ ሥፍራና ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይደረጋል።

## 6. የጾታ እኩልነት

ሴቶች በአገሪቱ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና የማህበራዊ ጉዳዮች ላይ የጎላ ተሳትፎ እንዲያደርጉ አስፈላጊው እገዛና ልዩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል። በወንዶችና በሴቶች መካከል የጾታ እኩልነት መብት በሕግም፣ በተግባርም ይከበራል። ለተመሳሳይ ሥራ እኩል ክፍያ የሚለው መርህ በሥራ ላይ ይውላል። እስካሁን የነበሩ መንግሥታት ከተስፋ የዘለለ ተግባር ባለመፈፀማቸው ሴቶች የደረሰባቸውን መድሎ ለማስቀረት በትምህርት፣ በሥራና በፖለቲካ ሠፊ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ልዩ ድጋፍ ይደረግላቸዋል።

## 7. የመገናኛ ብዙሓን ነፃነት

ሚዛኑን የጠበቀ የመረጃ ስርጭት ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈን ዓይነተኛ ዋስትና ነው። ጋዜጠኞች ሚዛኑን የጠበቀ ትክክለኛ ዜና ለሕዝብ የማቅረብ፣ ስለመንግሥት እንቅስቃሴና ስለፖለቲካው ሥርዓት ሂደትና አሰራር ያለፍርሃት በሀቀኝነት የመዘገብና የመተቸት መብት የተጠበቀ ይሆናል። የብዙሃን መገናኛ ተቋማት ተልዕኳቸውን ሊወጡ እንዲችሉ ከመንግሥት ተጽዕኖ ነፃ ሆነው ህብረተሰቡን እንዲያገለግሉ የሕግ ጥበቃ ይደረግላቸዋል።

## 8. የሃይማኖት እኩልነትና ነፃነት

የማናቸውም ሰው የአምልኮና የእምነት ነፃነት በሕግ የተከበረ ይሆናል። በሃይማኖትና በእምነት ምክንያት በመንግሥትም ሆነ በማንኛቸውም አካል ምንም ዓይነት ተጽዕኖ አይደረግም። መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ሆነው መንግሥት የሃይማኖት እኩልነትን ያከብራል፤ ያስከብራል።

## 9. የኢትዮጵያ አገራዊ አንድነት

የኢትዮጵያ ሕዝብ በመካከሉ ምንም ዓይነት የሃይማኖት፣ የቋንቋ፣ የብሔር/ብሔረሰብና ማንኛቸውም መድልዎ ሳይደረግበት፤ በእኩልነት፣ በመከባበር፣ በጋራ ጥቅምና ብልጽግና ላይ የተመሰረተ ዘላቂነት ያለው አንድነት ይኖረዋል። የኢትዮጵያ አገራዊ አንድነት ማለትም ሉዓላዊነቷና የግዛት አንድነቷ፣ ዓለም አቀፍ ድንበሯ የተከበሩና የማይደፈሩ ይሆናሉ።

## 10. ዕርቅና ሰላም

በኢትዮጵያ ብሔር/ብሔረሰቦች መካከል ጥላቻንና ግጭትን ለማጥፋት፤ ብሔር/ብሔረሰቦች ልዩነቶቻቸውን በአግባቡ ጠብቀውና ይዘው በሚያቀራርቧቸውና አንድ በሚያደርጓቸው ጉዳዮች ላይ የበለጠ እንዲያተኩሩ፤ ልዩነቶቻቸውንና ችግሮቻቸውንም በመከባበር፣ በመቻቻልና በመወያየት ፍጹም ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲፈቱ፤ በፖለቲካ ኃይሎች መካከል ብሔራዊ ዕርቅ እንዲወርድና በዜጎች መካከል ብሔራዊ መግባባት እንዲጠናከር ሕጋዊና መዋቅራዊ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ ይደረጋል።

# ክፍል III

# የኢኮኖሚ ጉዳዮች

## 11. ጠቅላላ

11.1 አገሪቱ ራሷን ከመመገብ አልፋ ልማትና ብልጽግና እንድታመጣ ትኩረት የሚሰጥ፣ የመላውን ሕዝብ የኑሮ ደረጃና ሕይወት የሚያሻሽል፣ ወደ ዘላቂና ሁለንተናዊ ካፒታሊስታዊ ዕድገት የሚያመራ የልማት ፖሊሲ ተግባራዊ ይሆናል።

11.2. የግል ክፍለ ኤኮኖሚን የሚያበረታታ በገበያ መርህ ላይ የተመሰረተ የኢኮኖሚ ሥርዓት ተነድፎ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል።

11.3. መንግሥት በኤኮኖሚው መስክ የሚኖረው ሚና በህግ የተወሰነ ሆኖ ለኢኮኖሚው ዕድገት መቀላጠፍ አጋዥ የሆኑ ፖሊሲዎችን የማውጣት፣ የመሠረተ ልማት አውታሮችን የመዘርጋት፣ ለሀገራዊ ዕድገትና ልማት የሚበጁ የኢንቨስትመንት ፖሊሲዎችን የማራመድ፣ የገበያ ኃይሎች እንዲጠናከሩና እንዲዳብሩ የማድረግ ኃላፊነት ይኖረዋል። የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚና የገበያ ውድድሩ በማይሸፍናቸው ሴክተሮች መንግስት በኢኮኖሚው ውስጥ በህግ የተገደበ ጊዜአዊ ተሳትፎ ይኖረዋል።

11.4 መንግሥት በህግ ከተቀመጠለት ሚና ውጭ በኢኮኖሚው ሥርዓት ጣልቃ እየገባ በማምረት፣ በማከፋፈልና በሽያጭ ተግባራት ውስጥ ገብቶ ከዜጐች ጋር በተወዳዳሪነት አይሰለፍም።

11.5 ከአገሪቱ ብሔራዊ ጥቅሞች ጋር በማይጋጭ ሁኔታ የውጪ ባለሃብቶች በኢኮኖሚ እንቅስቃሴው እንዲሳተፉ በማድረግ ዘመናዊ ቴክኖሎጂንና የስራ ክህሎትን ወደ አገር ቤት እንዲያስገቡ የሚያስችል ሁኔታ ይመቻቻል።

11.6 ለኢትዮጵያውያን በተለያዩ የኤኮኖሚ ዘርፎች ሠፊ የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ፣ የሕዝቡን የሥራና የቁጠባ ባህል የሚያሳድጉ ፖሊሲዎችና ስልቶች ይቀየሳሉ፣ ተግባራዊ ይደረጋሉ።

11.7 በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኘውን የህብረተሰብ ክፍል በማገዝ፤ የሀብታምና የደኃውን፣ የተማረውንና ያልተማረውን፣ የከተሜና የገጠሬውን የኑሮ ደረጃ የሚያሻሽሉና የሚያቀራርቡ ፖሊሲዎች ይቀየሳሉ፣ ተግባራዊም ይደረጋሉ።

11.8 ዜጎች ጉልበታቸውንና ንብረታቸውን በማቀናጀት አካባቢያቸውን ለማልማት በእርሻ፣ በኢንዱስትሪ፣ በንግድ፣ በማመላለሻ፣ በተፈጥሮ ሀብቶች ፍለጋና ምርት እንዲሁም ልዩ ልዩ ማህበራዊ አገልግሎቶችን በማቅረብና በማስፋፋት ተሳትፎ እንዲያደርጉ መንግሥት ሁኔታዎችን ያመቻቻል።

11.9 የፈጠራ ሥራዎች ይመዘገባሉ፣ የፈጠራ ባለቤቶችም መብት በሕግ የተከበረ ይሆናል። የፈጠራ ችሎታ ዳብሮ የኢኮኖሚን ግንባታ እንዲያግዝ መንግሥት ሁኔታዎችን በማመቻቸትና የፈጠራ ባለቤቶችን በማበረታታት ዐቢይ ሚና ይጫወታል።

11.10 የኮንስትራክሽን፣ የመንገድ፣ የትራንስፖርት፣ የመገናኛ፣ የመብራት፣ የማዕድን፣ የውሃና የመሳሰሉት የመሠረተ ልማት ግንባታዎች የሕዝቡን ጥቅምና የሀገሪቱን የልማት ፍላጐት በሚያሟላ መንገድ እንዲስፋፉ ይደረጋል።

## 12. ግብርና

12.1 የእርሻ ምርት ውጤት ከፍ እንዲልና በዓለም አቀፍ ደረጃም ተወዳዳሪነት እንዲኖረው የአርሶ አደሩን ምርታማነት በማሳደግ ሕይወቱን እንዲያሻሽል መንግሥት አስፈላጊውን የምርምር፣ የሥልጠና፣ የቴክኖሎጂና የባለሙያ ድጋፍ ያደርጋል።

12.2 የአገራችን ግብርና ከዝናብ ጥገኛነት ተላቆ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን ለሰፋፊ እርሻና ለመስኖ ልማት ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

12.3 የአርብቶ አደሩን ህብረተሰብ የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ተገቢውን ድጋፍ በመስጠት፤ በግብርናም ሆነ በዘመናዊ የእንስሳት እርባታ ሥራ መስክ ላይ የሚሰማሩበት ሁኔታዎች ይመቻቻሉ።

12.4 ለኢንዱስትሪው ሴክተር ግብዓት በመሆን በሚያገለግሉና ለውጭ ገበያ ሊቀርቡ በሚችሉ የተለዩ የግብርና ምርቶች ላይ ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

12.5 በልማት ወደ ኋላ ለቀሩ አካባቢዎች መንግሥት አስፈላጊውን ትኩረት በመስጠት ሁለንተናዊ ድጋፍና እገዛ እንዲያደርግላቸውና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ከአገሪቱ ሀብት ተካፋይ እንዲሆኑ ጥረት ይደረጋል።

12.6 ደን፣ አራዊት፣ ሸለቆ፣ ኲሬብታ፣ ተራራና የመሳሰሉት ሌሎች አገልግሎታቸው ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚዘልቅ የተፈጥሮ ጸጋዎች በመንግሥት ጥበቃ ሥር ሆነው እንክብካቤ ይደረግላቸዋል።

12.7 ሰፈራ እንደአስፈላጊነቱና በፈቃደኛነት ላይ በተመሰረተ ሁኔታ ተግባራዊ ይደረጋል።

## 13. የመሬት ይዞታ

13.1. አርሶ አደሮች በያዙት የእርሻ መሬት ላይ ባለቤትነታቸው በሕግ ተረጋግጦ በፍላጎታቸው የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማከራየት፣ የማውረስ፣ የማስተላለፍ መብታቸው እንዲጠበቅ ይደረጋል።

13.2 የከተማ ነዋሪዎች የመኖሪያ ቤትና ሌላ መሰረታዊ ግንባታ ያካሄዱበት የከተማ መሬት ላይ ያላቸው የባለቤትነት መብት በህግ ተረጋግጦ የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማከራየት፣ የማውረስና የማስተላለፍ መብታቸው ይከበራል።

13.3 አርብቶ አደሩ ህብረተሰብ ኑሮው በሂደት ወደ ቋሚ ሰፋሪነት እስኪቀየር ድረስ የሰፈረበት መሬት በመንግስት ወይም በጋራ (በcommunity) ይዞታነት ተይዞ የሚቆይ ይሆናል።

13.4 በገጠርም ሆነ በከተማ በጋራ ወይም በማህበር ባለቤትነት የሚያዝ መሬት ሊኖር ይችላል።

13.5 አርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች ያልሰፈሩበት የአገሪቱ መሬት ለጊዜው በመንግስት ባለቤትነት ተይዞ ይቆያል። በሂደት ለተለያዩ የህዝብ አገልግሎቶች፣ ለኢንቨስትሜንትና መሬት ለሌላቸው አርሶ አደሮች ፍትሀዊ በሆነ መልኩ ይከፋፈላል።

13.6 የእርሻ መሬት የግል ንብረት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ሰፋፊና ዘመናዊ እርሻዎችን፣ እርባታዎችንና የመሳሰሉትን የግብርና ተግባራት ለማካሄድ ለሚሹ በግል፣ በሽርክናና በማህበር ለተደራጁ ዜጎች መንግሥት መሬት በኪራይ ይሰጣል።

13.7 ማንኛውም የገጠርና የከተማ መሬት ለህብረተሰቡ የጋራ ጥቅም በራስ አስተዳደር ክልልም ሆነ በፌዴራል መንግስት ሲፈለግ ፍትሀዊ በሆነ መንገድ ካሳ ተከፍሎ ወይም ምትክ ተሰጥቶ እንዲለቀቅ የሚያስችል ፖሊሲ ስራ ላይ እንዲውል ይደረጋል።

# 14. ንግድና ኢንዱስትሪ

14.1 በዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኘው የኢንዱስትሪ ዘርፍ በአገር ውስጥና በውጪ አገር ባለ ሀብቶች ሰፊ ተሳትፎ እንዲገነባና እንዲያድግ፣ መንግሥት የኢንዱስትሪ ክፍለ ኢኮኖሚ የልማት እስትራቴጂ (Industrial Extension) አዘጋጅቶ የሕግና የማስተዋወቅ እርምጃዎችን በመውሰድ ላቅ ወዳለ የዕድገት ደረጃ እንዲሸጋገር ያደርጋል። በዚህ ዘርፍ በሚደረገው ጥረት የአገር ውስጥ ባለሀብቶችን የሚያበረታቱ ልዩ ልዩ እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

14.2 ለቱሪዝም ኢንዱስትሪ ተገቢ ትኩረት በመስጠት ለአገሪቱ ኤኮኖሚ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ለማበርከት የሚያስችሉ እርምጃዎች ይወሰዳሉ።

14.3 የአገሪቱ የከርስ ምድር ሀብቶች የመንግሥት ልዩ ጥበቃ እየተደረገላቸው በመንግሥትም ሆነ በግል ክፍለ ኤኮኖሚ የሚለሙበት ሁኔታ ይመቻቻል።

14.4 ማንኛቸውም ሰው ሸቀጣ ሸቀጦችንና አገልግሎቶችን በሀገር ውስጥም ሆነ ወደ ውጪ ሀገር በመላክ የመነገድ፣ የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የምርትና የሸቀጥ ልውውጥ የማዳበርና በአጠቃላይ ገበያን የማስፋፋት መብት ይኖረዋል፣ ሕጋዊ ጥበቃ ይደረግለታል።

14.5 አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች፣ የዕደ ጥበብ ሥራዎችና ሀገር በቀል ቴክኖሎጂዎች፤ በከፍተኛ ትኩረት እንዲስፋፉ ይደረጋል።

14.6 በመንግሥት እጅ የሚገኙ የልማት ድርጅቶች ከሀገሪቱ የገበያ ቶክክር ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ቀስ በቀስ ወደ ግል ይዞታነት እንዲተላለፉ ይደረጋል።

14.7 በገቢና በውጭ ንግድ ዘርፍ የአገሪቱ ባለሀብቶች በገበያ ሥርዓት መሠረት በዋናነት እንዲሳተፉና ኢኮኖሚውን እንዲያጐለብቱ ይደረጋል።

14.8 ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የንግድ ግዴታዎችን በመጠበቅ ከሌሎች አገሮች ጋር በተለይም ከጐረቤት አገሮች ጋር በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ የንግድ ግንኙነት እንዲኖራት ይደረጋል።

14.9 የማምረቻ፣ የአገልግሎት ሰጪና የንግድ ድርጅቶችን እንዲሁም የአርሶ አደሩንና የኢንዱስትሪ ሠራተኛውን ሥራ የሚያበረታታ የታክስና የግብር አከፋፈል ሥርዓት እንዲስፍን ይደረጋል።

14.10 ባንክና ኢንሹራንስን የመሳሰሉ የፋይናንስ ተቋማት የአገሪቱን ጥቅሞች በማይጐዳ ሥርዓት እየተመሩ በገበያ ህግ እንዲሰሩና በዘርፉም የግል ባለሃብቶች ተሳትፎ እንዲስፋፋ ይደረጋል።

# ክፍል IV

# ማህበራዊ ጉዳዮች

## 15. ትምህርት

15.1 የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት በዋናነት የአገሪቱን የተማረ (የሰለጠነ) የሰው ኃይል ፍላጐት በማሟላት ለሁለንተናዊ ልማትና ዕድገት አስተዋጽዖ የሚያደርግ፣ የሕዝቡን ታሪክና ባህል ያቀናጀ፣ የሣይንስና ቴክኖሎጂ ዕውቀትን የሚያስፋፋና አገሪቱን ወደ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ የሚያሸጋግር ሆኖ ይዘጋጃል። በትምህርት ፖሊሲና ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትም ሆነ አፈፃጸም መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ወላጆችና ባለሙያዎች ተገቢ ተሣትፎ ይኖራቸዋል።

15.2 የትምህርትን አገልግሎትና ሥርጭት በማስፋፋትና በማሻሻል፣ ይዘቱን በመወሠንና ጥራቱን በመጠበቅ ዋናው ሚና የመንግሥትና የሕዝብ ሆኖ በዚህ ረገድ የግሉ ሴክተር ከፍተኛ ድርሻ እንዲኖረው ይደረጋል።

15.3 ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለአገሪቱ የኢንዱስትሪና የቴክኖሎጂ ምጥቀት የሚኖራቸውን ከፍተኛ ድርሻ ግምት ውስጥ በማስገባት የተለየ ኢንቨስትመንት የሚደረግባቸው ብቻ ሣይሆን የማስተማርና የመመራመርን ሂደት በሚያጐለብቱበት ሁኔታ እንዲደራጁና ያካዳሚክ ነፃነታቸው ተጠብቆ እንዲሰሩ ይደረጋል። በተለይም ሀገሪቱ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንድትሆን ይደረጋል።

15.4 የቴክኒክ፣ የሙያና የዕደ ጥበባት ትምህርት ቤቶች በየአካባቢው እንዲከፈቱና እንዲጠናከሩ በማድረግ ሣይንስና ቴክኖሎጂ በከተማም ሆነ በገጠሪቱ ኢትዮጵያ እንዲስፋፉ ጥረት ይደረጋል።

15.5 ከመደበኛ ትምህርት በተጨማሪ ለጐልማሶች ትምህርት ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

15.6 የአገሪቱ የኢኰኖሚ ዕድገት እስከሚፈቅድ ድረስ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ቢያንስ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በነፃ የሚያገኝበት ሁኔታ ይፈጠራል።

## 16. ጤና

16.1 በሽታን አስቀድሞ በመከላከልና የጤና እንክብካቤ በማድረግ ላይ ያተኰረ የጤና አገልግሎት ሥርዓት ይዘረጋል።

16.2 በሁሉም የአገሪቱ አካባቢ በተለያየ ደረጃ የጤና አገልግሎት የሚቋቋምበትና ሁሉም ሕዝብ የአገልግሎቱ ተጠ ቃሚ የሚሆንበት ሁኔታ ይመቻቻል።

16.3 ዘመናዊ የሕክምና መሣሪያዎችና መድኃኒቶችን የሚያመርቱ ተቋማት በአገር ውስጥ እንዲደራጁና ፍቱን መድኃኒትነታቸው የተረጋገጠላቸው የባህል መድኃኒቶችም ሳይንሳዊ በሆነ ጥናትና አቀራረብ ተዘጋጅተው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ይደረጋል።

16.4 የግሉ ሴክተር በጤና አገልግሎት ዘርፍ ጉልህ ድርሻ እንዲኖረው ይደረጋል።

16.5 የተለያዩ ተላላፊና ወረርሺኝ በሽታዎችን ሥርጭት ለመቆጣጠርና ለመግታት ይቻል ዘንድ ሕዝቡን ያሳተፈ እንቅስቃሴ ይደረጋል።

16.6 ንጹህ የመጠጥ ውሃ ለሁሉም የአገሪቱ ሕዝብ እንዲዳረስ ይደረጋል።

## 17. ቋንቋ

17.1 የሁሉም ብሔር/ብሔረሰቦች ቋንቋ እኩልነት ይከበራል፣ እንዲዳብርም አስፈላጊው እገዛና ድጋፍ ይደረጋል።

17.2 ለጋራ መግባቢያ፣ ለጋራ ገበያ፣ ለሣይንስና ቴክኖሎጂ ልውውጥ አመቺ የሆነ ከአገሪቱ ብሔር/ብሔረሰቦች ቋንቋዎች መካከል አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆነ/ኑ ቋንቋ/ዎች የፌዴራል መንግሥቱ ኦፊሴላዊ የሥራ ቋንቋ/ዎች ይሆናል/ሉ፡፡

17.3 በፌዴራል ደረጃ የሚመረጥ/ጡ ቋንቋ/ዎች በሁለም የአገሪቱ ክልሎች በሚገኙ ት/ቤቶች በመደበኛ ትምህርትነት እንዲሰጥ/ጡ ይደረጋል፡፡ እንዳስፈላጊነቱም በማስተማሪያ ቋንቋነት ያገለግላል/ሉ፡፡

17.4 በፌዴራል ደረጃ የሚመረጥ/ጡ ቋንቋ/ዎች መኖሩ/ራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የራስ ገዝ ክልሎች ራሳቸው የሚመርጡት ቋንቋ የክልሉ መስተዳድር የሥራ ቋንቋ ይሆናል፡፡ በክልሉ ት/ቤቶችም የመግሪያና የማስተማሪያ ቋንቋ ይሆናል፡፡

17.5 በከተሞች፣ የነዋሪዎችን ብሔር/ብሄረሰባዊ ስብጥር ግምት ውስጥ ባስገባና በፍላጐት ላይ በተመሠረተ መልኩ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

## 18. ልዩ ልዩ ማህበራዊ ጉዳዮች

18.1 ከአገሪቱ ዕድገት ጋር ተመጣጥኖ በየደረጃው የሚዳብር ፍትሐዊ የዜጐች ማህበራዊ ደህንነት (Social Security) አገልግሎት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

18.2 ሥራ አጥነት ደረጃ በደረጃ ከኢትዮጵያ እንዲጠፋና ከእርሱም ጋር የተያያዙ ማኅበራዊ ችግሮች መፍትሔ የሚያገኙበት መንገድ ይመቻቻል፡፡

18.3 የወጣቶች መሠረታዊ ፍላጐቶች መማር፣ መስራትና መዝናናት እንደመሆናቸው እነዚህን ፍላጐቶቻቸውን የሚያሟሉበት ፖሊሲ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

18.4 ህፃናትና ወጣቶች በሚማሩባቸው ት/ቤቶች አካባቢ ሱስ የሚያስይዙ አደገኛ እፆችና የአልኮል መጠጦች የሚሸጡባቸው ድርጅቶች በቅርበት እንዳይኖሩ የሚያደርግና ዕድሜው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ታዳጊዎችና ወጣቶች እነዚህን አገልግሎቶች ገዝተው እንዳይጠቀሙ የሚያደርግ ህጋዊ አሰራር ይዘረጋል፡፡

18.5 በኅብረተሰቡ ዘንድ ጐጂ ልማዶችን ለማስወገድ የሚያስችል የአመለካከትና የአስተሳሰብ ለውጥ ለመፍጠር ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፡፡

18.6 የአገራችንን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ከሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ለመቆጣጠር የሚያስችልና በኅብረተሰቡ ዘንድ የአመለካከት ለውጥ የሚፈጥር የሥነ ሕዝብ ፖሊሲ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ጉዳዩን በኃላፊነት የሚመራ አገራዊ ተቋምም እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡

18.7 የአገሪቱ ጠቃሚ ባህሎች፣ ታሪካዊ ሥፍራዎች፣ ሥነ ጽሑፎች፣ የሃይማኖትና የባህል ቅርሶች ተከብረውና ተጠ ብቀው ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተላለፉ ይደረጋል፡፡

18.8 በመንግሥትና በሕዝብ አገልግሎት ሥራ ላይ በቂ አገልግሎት የሰጡ ዜጐች አቅም በፈቀደ ከወቅቱ የኑሮ ሁኔታ ጋር የተመጣጠነ የጡረታ ዋስትና እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡

18.9 ለሀገር አንድነትና ለሕዝብ ሉዓላዊነት መከበር ሲሉ ጀብዱ የፈፀሙ ብሔራዊ ጀግኖች በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ በሳይንስ፣ በትምህርት፣ በስፖርት፣ በኪነ ጥበብና በሌሎች ጉዳዮች ለሀገር እድገት ልዩና ምስጉን አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ ዜጐች እውቅና፣ ልዩ ልዩ ክብርና ሽልማቶች እንዲሁም ኑሮአቸውን የሚያግዝ ጥቅማ ጥቅም የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

18.10 ለሕፃናት፣ ለእናቶች፣ ለአረጋውያን ወዘተ. ከአገሪቱ የኢኰኖሚ አቅም ጋር የተመጣጠነ ልዩ እንክብካቤ ይደረጋል፡፡

18.11 በልዩ ልዩ ምክንያት ከአገራቸው ተሰደው ያሉ ኢትዮጵያዉያን ወደ አገራቸው ተመልሰው ሰላማዊ ሕይወት እንዲመሩ ይደረጋል፡፡ አቅም በፈቀደ መጠን መንግሥት ተገቢውን ድጋፍ ያደርግላቸዋል፡፡

18.12 ከኢትዮጵያዊያን የተወለዱ ነገር ግን ነዋሪነታቸው ከኢትዮጵያ ውጭ የሆነና የሌላ አገር ዜግነት የወሰዱ ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጣምራ ዜግነት የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

18.13 በኢንዱስትሪው ዘርፍ ወሳኝ ሚና የሚኖረውን የሠራተኛውን ሕዝብ ተገቢ ጥቅም የሚያስጠብቅ ሚዛናዊ የአሰሪና ሠራተኛ ሕግ እንዲኖር ይደረጋል። እንዲሁም ሠራተኛው ለኑሮው በቂ የሆነ ክፍያ የሚያገኝበት ሁኔታና ለጤንነቱና ለሕይወቱ ተገቢ ዋስትና እንዲያገኝ ይደረጋል።

18.14 የመኖሪያ ቤት ለመሥራት አቅም የሌላቸውን ዜጐች የመኖሪያ ቤት ችግር ለማቃለል የሚያስችል የኢንቨስትመንትና የመተጋገዣ ተቋሞች/አገልግሎቶች ስር□ት ይዘረጋል።

18.15 በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ የተጐዱ፤ ከቄያቸው፣ ከአገራቸውና ከቤታቸው የተፈናቀሉ ዜጎችን መልሶ ለማቋቋም ጥረት ይደረጋል።

18.16 ለሁለንተናዊ ዕድገታችን ከፍተኛ ዕንቅፋት በመሆን ላይ ያለውን ሙስና ለማስወገድ እንዲቻል ለሙስና ዕድል የሚከፍቱ የአሰራር ስርዓቶችን ለመቀየር፣ የተጠናከረ የቁጥጥርና የክትትል ተግባር ለማከናወን የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ ሥራ ላይ ይውላል።

18.17 በደርግም ሆነ በኢሕአዴግ ያላግባብ የተወረሱ ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ለሕጋዊ ባለቤቶቻቸው በጥናት በተደገፈና የተለያዩ አማራጮችን ግምት ውስጥ ባስገባ የአፈጻጸም ስርዓት እንዲመለሱ ይደረጋል።

# ክፍል V

# የውጭ ግንኙነት፣ የመከላከያ፣ የፖሊስና የደኅንነት ጉዳይ

## 19. የውጭ ግኑኝነት

19.1 የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ የብሔራዊ ጥቅሞችዋ ማራመጃ መሣሪያ ሲሆን፤ ከማንኛውም አገርና መንግሥት ጋር በእኩልነት፣ በጋራ ጥቅም፣ በውስጥ ጉዳይ ጣልቃ ባለመግባትና በመከባበር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ይደረጋል። በተለይም ከጐረቤት አገሮች ጋር ቅርበት ያለው የወዳጅነት፣ የትብብር፣ የመተጋገዝና የጋራ ዕድገት ግንኙነቶች እንዲፈጠሩና እንዲመቻቹ፤ በሰላም፣ በልማትና በዕድገት ጐዳና እየተደጋገፉ እንዲጓዙ ልዩ ጥረት ይደረጋል።

19.2 የአገሪቱ የዲፕሎማሲ ጥረት በዋናነት የአገሪቱን በጎ ገጽታ በመገንባት፣ የውጭ ንግድን በማስፋፋትና የውጭ አገር ኢንቨስተሮችን በመሳብ ላይ እንዲያተኩር ይደረጋል።

19.3 በውጪ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሰብዓዊ መብታቸው እንዲከበርና ጥረው ግረው ያፈሩት ሃብታቸው እንዲጠበቅ አስፈላጊው ጥረት ያደርጋል።

19.4 ለኢትዮጵያ የባህር በር ባለቤትነት መብት ማንኛውም ዓይነት ሰላማዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ዲፕሎማሲያዊና ሕጋዊ ጥረቶች ይደረጋሉ።

## 20. መከላከያ

20.1 የአገሪቱ መከላከያ ሰራዊት ለህገ መንግሥት ተገዥ የሆነ፣ ለኢትዮጵያ ዳር ድንበርና ሉዓላዊነት መጠበቅ፣ ለሕዝቡ ሠላምና ደህንነት መከበር የቆመ ሠራዊት መሆን በሚያስችለው መልኩ ይደራጃል።

20.2 የመከላከያ ሠራዊት በጥንቅሩ ከሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጣ ሆኖ በሎጂስቲክና በዘመናዊ መሣሪያ የተጠናከረ፣ የሙያ ብቃት ያለው፣ ዘመናዊና ግዳጁን ለመወጣት ዝግጁ የሆነ ኃይል እንዲሆን ይደረጋል።

20.3 የሀገሪቱ የመከላከያ ኃይል፤ በሕዝብ የመብት ጥያቄ ላይ ጣልቃ የማይገባ፣ ከማናቸውም የፖለቲካ ተሳትፎ በህግ የተገለለ እንዲሆን ይደረጋል።

20.4 ሕዝብ የአካባቢውን ሠላም በማስከበርና አገሩን ከማናቸውም ጥቃት በመከላከል ረገድ ንቁና የተደራጀ ተሣትፎ እንዲኖረው የሚያስችል ስርዓት ይዘረጋል።

## 21. ፖሊስና ደህንነት

21.1 የአገሪቱ የፖሊስና የደህንነት ኃይል የአገርን ደህንነትና የህዝብን ሠላማዊ ኑሮ የሚያስከብር፣ ለህገ መንግሥት ታማኝ የሆነ ኃይል ሆኖ ይደራጃል።

21.2 የፖሊስና የደህንነት ኃይሉ ከሁሉም የአገሪቱ ክፍል የተውጣጣ ሆኖ፤ ሕዝብን ለማገልገል የሚያስችል ሥነ ምግባር የተላበሰና ህግና ፍትህን ለማስፈፀም የሚያስችል የሙያ ብቃት ያለው ኃይል እንዲሆን ይደረጋል።

21.3 የፖሊስና የደህንነት ኃይሉ ከማናቸውም የፖለቲካ ተሳትፎ በህግ የተከለከለና በሕዝብ የመብት ጥያቄ ላይ ጣልቃ የማይገባ፣ እንዲሆን በማድረግ የአገርንና የህዝብን ደህንነት እንዲጠብቅ ይደረጋል።

21.4 እያንዳንዱ የራስ አስተዳደር ክልል መንግሥት ለክልሉ ሕዝብ ሠላምና ደህንነት ጥበቃ የፖሊስና የአካባቢ ጥበቃ ኃይል ሊያቋቁም ይችላል።

**ጥር 24 ቀን 2001 ዓ.ም**

**በተደረገ 4ኛ ድርጅታዊ ጠቅላላ ጉባዔ ተሻሽሎ የጸደቀ**